# ስነ-ምህዳራዊ የከተማ ግብርና መልካም ተሞክሮ በአዲስ አበባ




<u>አዘጋጆች፡-</u>

- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)
- ነፃነት ገነነ
- ብርሃኑ ሓጎስ
- ልደት ሰለሞን
- አለም ፀጋይ



ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ታህሳስ 2014 ዓ.ም.

# ስነ-ምህዳራዊ የከተማ ግብርና መልካም ተሞክሮ በአዲስ አበባ

**አዘጋጆች**

- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)
- ነፃነት ገነነ
- ብርሃኑ ሓጎስ
- ልደት ሰለሞን
- አለም ፀጋይ

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
ታህሳስ 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

## ህትመት

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም እና ምርጥ ተሞክሮ ማህበር

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 171 ኮድ 1110፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር፡- +251-911-246046/978-815102

ፋክስ ቁጥር፡- +251-116-686724

ኢ.ሜይል አድራሻ፡-

hailuara@yahoo.com; pelumethiopia@gmail.com

© ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም፣ 2014

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር ጋር በመሆን ይሄን የፕሮጀክት ሃሳብ በመሬት ላይ እንዲተገበር እና እንዲታተም የተደረገው በBread for the World/ PADD የገንዘብ ድጋፍ በመሆኑ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

መፅሃፍ አርታኢ፡- ዮሴፍ ጋረደው

የሽፋን ዲዛይን፡- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)

| ተ.ቁ | ቢጋር | ገፅ |
|---|---|---|
| 1. | **መግቢያ** …………………………………………………….. | 01 |
| 1.1 | የከተማ ግብርና ማለት ምን ማለት ነው? ……………….. | 01 |
| 2. | **የከተማ ግብርናን መተግበር የሚሰጠው ጥቅምና አስፈላጊነት** ……………………………………………….. | 03 |
| 2.1. | የከተማ ግብርና ጥቅም ……..………………………. | 03 |
| 2.2. | የከተማ ግብርና አስፈላጊነት ………………………………. | 04 |
| 3. | **የከተማ ግብርና አይነቶች እና አተገባበር** ………………… | 06 |
| 3.1. | የከተማ ግብርና አይነቶች ..……………………………. | 06 |
| 3.2. | የከተማ ግብርና አተገባበር ……………………………... | 07 |
| 4. | **የከተማ ግብርናን ለመተግበር ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች** ……………………………………………… | 08 |
| 4.1 | በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ስራ ላይ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች…………………………………………… | 08 |
| 4.2 | በመኖሪያ ግቢ ውስጥ ለሚደረጉ የጓሮ አትክልት ስራ ለመተግበር ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች ………. | 09 |
| 5. | **የከተማ ግብርናውን ስራ የተከተለው አካሄድ** …………… | 11 |
| 6. | **የተገኙ ውጤታማ ስራዎች** …………………………….. | 12 |
| 6.1. | መግቢያ …………………………………………………… | 12 |
| 6.2. | የተሰጡ ስልጠናዎች ……………………………………… | 13 |
| 6.3. | በወረዳው ላይ የከተማ ግብርና በመተግበሩ የተገኙ ውጤቶች ……………………………………………………. | 24 |
| 7. | **ስኬታማነት በከተማ ግብርና** ..…………………….…… | 26 |
| 7.1. | መግቢያ …………………………………………………… | 26 |
| 7.2. | ምሳሌዎች …………………………………..……………. | 27 |
| 7.3. | ቨርሚ-ኮምፖስት በከተማ ቆሻሻ ቅነሳ …………………… | 35 |
| 7.4. | መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት ………………………… | 36 |
| 7.5. | ታዳጊ እና ወጣት ተማሪዎች ……………………………… | 39 |
| 8. | **ከፕሮጀክቱ ምን ተማርን** ………………………………… | 45 |
| 9. | **ማጠቃለያ እና ምክረ-ሃሳብ** ………………………………. | 47 |
| 9.1 | ማጠቃለያ ………………………………………………… | 47 |
| 9.2 | ምክረ-ሃሳብ ……………………………………………….. | 47 |
| 10. | **ማጣቀሻ** …………………………………………………. | 48 |

# ምስጋና

ፔለም ኢትዮጵያ ይህንን ውጤታማ ስራ ተከትሎ የተዘጋጀውን ህትመት በማስመልከት በግቢያቸው ላይ ለተገሩት የህብረተሰብ ክፍሎች፣ እገዛ ላደረጉ የመንግስት አካላት፣ ግለሰቦች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ላበረከቱት ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ልባዊ ምስጋናውን እንደሚከተለው ያቀርባል፡፡

አንደኛ እና ዋነኛው በየካ ክፍለ ከተማ ውስጥ የወረዳ 10 የተወሰኑ ነዋሪዎች በቀላል ስልጠና እና የመስክ ጉብኝት ብቻ በመነሳሳት ይሰራል ተብሎ የማይገመተውን ውጤታማ የልማት ስራ በተግባር ሰርተው በማሳየታቸው እና ለሌሎች ነዋሪዎች ምሳሌ በመሆናቸው ላቅ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ሁለተኛ ይሄን ስራ እዚህ ቦታ ላይ ቢሞከር የተሻለ ይሆናል ብለው በመምከር እዚህ ወረዳ ላይ እንድንሰራ ምክራቸው ለለገሱን ለአአ ከተማ መስተዳድር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ፅ/ቤት እና ለየካ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና ግብርና ልማት ፅ/ቤት እንዲሁም የወረዳ 10 የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ፅ/ቤት አካላት እና ባለሙያዎች ላደረጉት ላልተቆጠበ እና ቀናነት የተሞላበት አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ምስጋና ሳቀርብ ደስታ ይሰማኛል፡፡

በስተመጨረሻ ስራው በተሳካ ሁኔታ ግብ ላይ እንዲደርስ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው Bread for the World ወይም ምግብ ለዓለም የተባለውን አጋር ድርጅት ሳመሰግን በተለይ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ ተወካይ ሚ/ር ክርስቶፍ ሽናይደር፣ ወ/ሪት ፅዮን ታደሰ፣ አቶ በቀለ ሙላት፣ አቶ ዳዊት ሰለሞን፣ ወ/ሪት ትግስት ወንድምአገኘሁ፣ እንዲሁም የድርጅቱ ሰራተኞች ላደረጉልን ከገንዘብ ባሻገር ሁለገብ ድጋፍ፣ ማበረታቻ እንዲሁም ምክር ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁኝ፡፡

ሃይሉ አርአያ ተድላ (ዶ/ር)
ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ግብርና ኤክስቴንሽን ዘርፍ በፔለም ኢትዮጵያ፣ ቤስት ፕራክቲስ አሶሴሽን አገር በቀል ድርጅት እና በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 በጓሮ አትክልት ልማትና በተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት በቤተሰብ ደረጃ ምግብ ዋስትና በማረጋገጥ፣ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛና የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዓላማ በማንገብ ተጠቃሚዎችን በመለየት፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠት አስፈላጊውን ግብዓቶችን በማቅረብ የቅርብ ድግፍና ክትትል በማድረግ ውጤታማና ተምሳሌታዊ ሥራ በተግባር ሠርተው ማሳየት በመቻላቸው እና ጠንካራ የልማት አጋራችን በመሆናቸው ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በዚህ ሥራ በባለቤትነት ስሜት ሲሳተፉ የነበሩ የክፍለ ከተማና የወረዳ አመራር እና ባለሞያዎች እንዲሁም ለፔለም ኢትዮጵያ አመራር እና ባለሞያዎች ለነበራቸው የላቀ ሚና ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አቶ አብርሃም ብርሃኑ
አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ግብርና ኤክስቴንሽን
እፅዋት ልማትና ጥበቃ ቡድን
አዲስ አበባ

# የስነምህዳራዊ የከተማ ግብርና መልካም ተሞክሮ

## መቅድም

ይህ ፅሁፍ የሚያትተው በከተማ አካባቢ የተደረገ ጤናማ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ስራ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበረሰብ የሚታወቀው በሸማችነቱ ነው፡፡ ቢሆንም ምርቱ ከየት እንደሚመጣ ብዙም ግንዛቤ የለውም፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ የሚቀርቡ አብዛኛዎቹ የጓሮ አትክልቶች ንፅህናው ካልጠበቀ ውሃ እና አፈር ብቻ ሳይሆን በአያያዝ የተበላሸ ምርትም ይቀርባል፡፡

የሚቀርቡ የእርሻ ምርቶች ከምግብነት ባሻገር ተረፈ ምርታቸው በተገቢው ጥቅም ላይ ስለማይውል ቆሻሻው ገኖ ለአካባቢ ንፅህና መበላሸት እና ጤና መታወክ ዋና ምክንያት እየሆኑ ነው፡፡

በሌላው አንፃር ደግሞ ከህዝብ ቁጥር አኳያ ብዙ ባይሆኑም ጤናማ የጓሮ አትክልት አምራች ቤተሰቦች ደግሞ አሉ፡፡ የቦታ ጥበት ሳይበግራቸው የራሳቸው አዳዲስ ፈጠራ በመጠቀም የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች የሚያመርቱ አሉ፡፡ ከዚያ አልፎም የከተማ ቆሻሻ ወደ ጥቅም የቀየሩ ሰዎች እና ቤተሰቦችም አሉ፡፡ ይህ የከተማ ግብርና መልካም ተሞክሮ በማስፋፋት የሃገራችን ከተሞች የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ይረዳል፡፡

ታሪኩም በዋናነት የሚያጠነጥነው የከተማ ግብርና በውስን በጀት እና ስልጠና ያስመዘገበው የኘሮጀክት መልካም ተሞክሮ ነው፡፡ የBread for the world/ የገንዘብ ድጋፍ በፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርቲየም በኩል "የሥነ ምህዳራዊ ግብርና አማካኝነት ማስፋፋት" በሚባለው ኘሮጀክት ብዙ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ ምርጥ ተሞክሮ ማህበርም የስኬታማ ስራ መለኪያ የበጀት መጠን ሳይሆን ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚያደርስበት አካሄድ ነው ብሎ ያምናል፡፡

የዚህ ህትመት ጥንቅር እና ህትመት ሊሳካ የቻለው በBread for the world በሚባል ለጋሽ ድርጅት ቀና ድጋፍ በማድረጉ ነው፡፡

አስራት መንገሻ
የፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርቲየም የቦርድ ሊቀመንበር
አዲስ አበባ; ኢትዮጵያ
ታህሳስ 2014

# 1. መግቢያ

## 1.1 የከተማ ግብርና ማለት ምን ማለት ነው?

የከተማ ግብርና በአለማችን ላይ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ቀላል በሆነ መልኩ ለአካባቢው አመቺ የሆኑ የግብርና ስራዎች የሚተገበሩበት ዘርፍ ሲሆን በመተግበሩም ምክንያት ነዋሪዎች ጤናማ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ትኩስ ምርቶችን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ አቅርቦቱ እንዲኖራቸው፤ የኑሯቸው ሁኔታ እንዲሻሻል እንዲሁም የማህበረሰቡን የምግብ ዋስትና ከማስጠበቅ ባለፈ ለስነ-ምግብ ይዘት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡

ይህም በመሆኑ አብዛኛው የከተማ ነዋሪ በቀላሉ የከተማ ግብርናና በግቢያቸው ውስጥ ባለ ባዶ መሬት ላይ፣ ያገለገሉ ወይም የወዳደቁ እቃዎችን ለምሳሌ ጀሪካን፣ ማዳበሪያዎች፣ ጆንያዎች፣ የውሃ መያዣ ኮዳዎች፣ ወዘተ በመጠቀም እንዲሁም ግቢያቸው በስሚንቶ የተሰራ ቢሆንም በብሎኬት የተወሰነ የአትክልት መስሪያ ቦታ በማመቻቸት ወይም በመጠቀም በቀላሉ ማምረት ሲሆን ከቤተሰብም አልፎ የከተማውን ማህበረሰብ በተሻለ መንገድ መመገብ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ በአለም ላይ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች የከተሞች እድገት መስፋፋት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይህም ደግሞ በፊት ለግብርና ይውል የነበረ የእርሻ መሬት በአብዛኛው ለከተማ ማስፋፊያነት እየዋለ በመሆኑ የከተማ መስፋፋቱ በተወሰነ መልኩ ግብርናው ላይ እንዲሁም ሀገራዊ የምግብ ዋስትናን በማስጠበቁ በኩል አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀገራት ቅጥ ካጣው የከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ እየመጣ ያለውን ችግር ለመፍታት ያስችል ዘንድ የከተማ ግብርናን በስፋት ለመተግበርና በዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ትኩረት ሰጥተው የተለያዩ ስራዎች በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሀገራችን በተለይ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የከተማ ግብርናን መተግበር ከሌሎች ሙያዎች ባልተናነሰ መልኩ ለህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል አይነተኛ የሆነ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተያይዞም በቂ ያልሆነ የግብርና ምርት አቅርቦት ችግር በስፋት እየታየ በመሆኑ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ግብርናና የአርሶአደር ልማት ኮሚሽን በማቋቋም "ምግባችን ከደጃችን" የሚል መፈክር አንግቦ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ያለ መሆኑ፤ እንዲሁም በተሻለ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታና ተነሳሽነቱ እንደመልካም ጅማሬዎች የሚታዩ ቢሆኑም አሁንም መስተካከል በሚገባቸው ተግዳሮቶች ላይ ፈጣን የእርምት እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ በ2012 ዓ.ም የኮቪድ-19 ወረርሺኝ በተከሰተ ግዜ አብዛኛው የማህበረስብ ክፍል ከከተማ ግብርና ጋር ተያይዞ በየቤቱ የሰራቸው ስራዎች ይበል የሚያሰኙና ተስፋ ሰጪ ሲሆኑ ዘርፉ ላይም የተሻለ ስራ መስራት እደሚቻል እንዲሁም ሀገራዊ የምግብ ዋስትናን ከማሻሻልና ከማስጠበቅ አንፃር አይነተኛ ሚና እንደሚኖረው ጥሩ አመላካች ሆኖ ቀጥሏል፡፡

# 2. የከተማ ግብርናን መተግበር የሚሰጠው ጥቅምና አስፈላጊነት

## 2.1 የከተማ ግብርና ጥቅም

በሀገራችን በሚገኙ ከተሞችም ሆነ ከፊል ከተማነትን የተላበሱ አካባቢዎች ላይ የከተማ ግብርና በተገቢው መንገድ ሲተገበር ለአምራቹም ሆነ ለሸማቹ የማህበረሰብ ክፍል ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ በአጠቃላይ የከተማ ግብርና ስራዎች ከሚሰጡት ጥቅሞች መካከል ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡ እነሱም፡-

- በአነስተኛ ወጪ፣ ትኩስ፣ ጤናማና የተመጣጠነ ምግብ እንድንመገብ ያስችለናል፡፡
- የመኖሪያ ግቢን እንዲሁም የአካባቢ ውበትን በመጠበቅ ሰዎች የዕለት ተለት ስራቸውን እና ውሏቸውን በተነቃቃ መንፈስ እንዲያሳልፉ ያስችላል፡፡
- የአረንጓዴ ሽፋንን ከፍ በማድረግ በከተማው የሚስተዋለውን ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንዲቀንስም ጉልህ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- ስራ አጥነት እንዲቀንስ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡
- ከተሞች በመስፋፋታቸው የተነሳ ለእርሻ የሚውሉ ታራሽ መሬቶች በመቀነሳቸው የሚከሰተው የመሰረታዊ ምግቦች እጥረት እና የዋጋ ውድነትን ለመቀነስ ያስችላል፡፡
- የከተማ ግብርናን በስፋት መተግበር ከውጭ ተገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የግብርና ውጤቶች ላይ የሚጠይቀውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡
- በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ተቀነባብረው ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ለሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ድጋፍ ያበረክታል፡፡

## 2.2 የከተማ ግብርና አስፈላጊነት

በአሁኑ ወቅት በዘርፉ ባለሙያዎችና በተጠቃሚው ማህበረሰብ በኩል ትልቅ ተስፋ ከተጣለባቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኛው የወደፊቱን የግብርና ስርዓት ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው፡፡ በየግዜው በሚያስደነግጥ ሁኔታ እየታየ ያለውን የእርሻ መሬት መቀነስ እና ከአለማችን ከፍተኛ የህዝብ እድገት ጋር ተያይዘው የሚታዩ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት በስፋትና በጥራት መተግበር አለባቸው ከሚባሉት አንዱ የከተማ ግብርና ነው፡፡ በተጨማሪም አለማችን ሀገራችንን ጨምሮ፤ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በሰብሎች ምርትና ምርታማነት ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳቶችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች ያልተጠቀሱ ተያያዥ ችግሮችን ለመቀነስ እንዲቻል የከተማ ግብርና በስፋት በማህበረሰቡ እንዲተገበር ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተገቢ መንገድ መስራት በሚፈልጉ አካላት እንዲተገበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የከተማ ግብርና አስፈላጊነትን ከሚያሳዩ ነጥቦች መካከል የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና እንዲሻሻልና እንዲረጋገጥ ያስችላል፡፡
- ቤተሰብን ጤናማ እና ትኩስ አትክልቶችን በየዕለት የምግብ ስርዓታቸው ውስጥ እንዲያገኙ ያግዛል በዚህም ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- የሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲያድግም ሆነ በራስ መተማመናቸው እንዲጎለብት ያግዛል፡፡
- የስራ እድልን ለወጣቶች ብሎም ለሴቶች ለመፍጠር ያስችላል፡፡
- የቤተሰብን ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማሳደግ እንዲሁም የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡

- በከተማ ውስጥ በቂ የሆነ የአትክልት አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል፡፡
- በከተሞች በተደጋጋሚ የሚያጋጥመውን የአቅርቦት ችግርን ለማቃለል ይረዳል፡፡
- ህብረተሰቡ አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ እንዲቆጠብ እድል ለመፍጠር ያስችላል፡፡

# 3. የከተማ ግብርና አይነቶች እና አተገባበራቸው

## 3.1 የከተማ ግብርና አይነቶች

የከተማ ግብርና አይነቶች በአምስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

1. **የእንስሳት እርባታ፡-** የዶሮ እርባታን፣ የበግ እና ፍየል እርባታን፣ የንብ እርባታን፣ የአሳ እርባታን፣ የወተት እርባታን እና ከብት ማደለብን ያካተተ ሲሆን ይህንንም ለመተግበር ሰፋ ያለ መሬት ይፈልጋል ሆኖም የንብ፣ የዶሮ፣ የፍየልና በግ እርባታ በቀላሉ በከተማ ነዋሪዎች ሊተገበር ይችላል፡፡
2. **የሰብል ምርት፡-** በከተማ ዙሪያ አካባቢ በሚገኙ አምራች ገበሬዎች የሚተገበር ሲሆን የምርት ሂደቱም ሰፋ ያለ መሬት ይጠይቃል፡፡ ይህ በመሆኑም በከተማ ዙሪያ የሚገኙት አምራቾች በሀገሪቱ ላይ የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ የሚታወቅ መመሪያ ባለመኖሩ ለስራው ያላቸውን ተነሳሽነት ከመቀነስም አልፎ ስጋት እንዲያድርባቸው አድርጓቸዋል፡፡
3. **የእንጉዳይ ምርት፡-** በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ያለው እና በጣም አነስተኛ በሆነ ንፁህ ክፍል ውስጥ የሚመረት ነው፡፡
4. **የቅመማ ቅመም ምርት፡-** የቅመማ ቅመም፣ የእፀዋት መድሃኒት፣ ወዘተ የአመራረት ሂደታቸው ከአትክልትና ከማስዋቢያ ያመራረት ሂደት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለቤተሰብም ጥሩ የገቢ ምንጭ እንዲሁም ለምግብ ፍጆታ መሆን ይችላሉ፡፡
5. **የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርት፡-** የተለያዩ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን፣ የማስዋቢያ እፅዋቶችን እንዲሁም የተለያዩ ችግኞችን የማምረት ሂደት ሲሆን በመሬት ስፋትና መጠን ላይ የሚወሰን የማምረት ዘዴ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ የከተማ ግብርናን ለመተግበር በጣም ተመራጭና ተስማሚ ነው፡፡

## 3.2 የከተማ ግብርና አተገባበር

የከተማ ግብርና በማንኛውም እድሜ ክልል ለሚገኙ የከተማው ነዋሪዎች በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፡፡ የከተማ ግብርና የተለያዩ ፈጠራዎችን በመጠቀም በማንኛውም የመሬት ይዞታ ሊተገበር ስለሚችል ማንኛውም ነዋሪ የከተማ ግብርናን ሊሰራ ይችላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት 40 በመቶ የሚሆኑ የከተማ ነዋሪዎች አነስተኛ በሆነ የመሬት ይዞታ ላይ የተለያዩ አትክልቶችን በቀላሉ ማምረት እና እንስሳቶችን ማርባት በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢ የተለመደ ተግባር ሆኗል፡፡

የተለያዩ ሰዎች የጓሮ አትክልቶችን፣ ቅመማ ቅመሞችን እንዲሁም ለማስዋቢያ የሚሆኑ እፅዋቶችን በግቢያቸው ውስጥ ከስር የተመለከቱትን ዘዴዎች በመከተል ያመርታሉ፡፡

- ባላቸው አነስተኛ የመሬት መጠን ልክ አቅደው ይተክላሉ፡፡
- ቀጥታ ወደላይ (ቨርቲካል) ወይም ተንጠልጣይ የአመራረት ዘዴን በመጠቀም የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን ያመርታሉ፡፡
- የተለያዩ የወዳደቁ መያዣ እቃዎችን በመጠቀም ያመርታሉ፡፡
- አካባቢን ከብክለት በመታደግ ከኩሽና የሚወጡትን እና የከተማ ቆሻሻችን ወደ ማዳበሪያነት ያመርታሉ፡፡
- በከተማ አካባቢ የሚታየውን የውሀ እጥረት ታሳቢ በማድረግ ውጤታማ የውሃ አጠቃቀምን በመጠቀም ያመርታሉ፡፡

# 4. የከተማ ግብርናን ለመተግበር ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች

## 4.1. በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ስራ ላይ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 4.1.1 ምቹ ሁኔታዎች

በከተማ ግብርና ስራ ላይ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች በጥቂቱ

- ህብረተሰቡ የኑሮ መወደድ እና የግብርና ውጤቶች ጤናማነት አጠራጣሪ መሆን ምክንያት በከተማ ግብርና ልማት ላይ የመስራት ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ፡፡
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለዘርፉ የሰጡት ትኩረት እንዲሁም መሬት ላይ የማውረድ እንቅስቃሴዎች መሻሻሉ፡፡
- የኮረና በሽታ በሀገራችን መስፋፋቱ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በቤት ውስጥ ስለሚያሳልፍ በበጎ ጎኑ የከተማ ግብርና ለመስራት ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ፡፡
- ከየቤቱ የሚሰበሰበውና የሚወገደው ደረቅ ቆሻሻ በከፍተኛ ሁኔታ መኖሩ ለአፈር ለምነት የሚያገለግሉ ግብአቶች በቀላሉ ማግኘት መቻሉ፡፡
- ከየቤቱ በጣም ያልተበከለ እና በቀላሉ መጣራት የሚችል ውሃ መኖሩ ለከተማ ግብርና ግብአት የሚሆን መሆኑ፡፡
- ከፍተኛ የአቅርቦት ክፍተት መኖሩ እንዲሁም ምርቶቹ የሚሸጡበት ሰፋፊ የገበያ እድሎች የፈጠረ መሆኑ፣ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

### 4.1.2. ተግዳሮቶች

በከተማ ግብርና ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በጥቂቱ

- ሻጭና ገዢ በቀጥታ የሚገናኙበት ጠንካራ የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

- ከፍተኛ በሆነ የህዝብ ቁጥር እድገትና በከተሞች መስፋፋት ምክንያት ህብረተሰቡ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ መሆኑና የምግብ ዋስትና ችግር እና ስራ-አጥነት መስፋፋቱ፤
- ግልፅ የሆነ የከተማ መሬት አጠቃቀም፤ የከተሞች ልማት በተለይ የከተማ ግብርና እቅድ አለመኖሩ፤
- ለእያንዳንዱ የከተማ ግብርና ዘርፍ የሚያስፈልግ አቅርቦትና የቴክኖሎጂ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ መታየቱ፤
- በሀገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች መሰረት ግልፅ በሆነ መልኩ ድጋፍ አለመደረጉ እና ቁርጠኛ የሆነ ፖለቲካዊ ይሁንታ አለመሰጠቱ፤
- ዘርፉን ለማሳደግና ለማዘመን እንዲሁም ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ሊያደርግ የሚችል አሰራር ወይም ትግበራ አለመታየቱ፤ እንደተግዳሮት የሚታዩ ናቸው።

## 4.2 በመኖሪያ ግቢ ውስጥ የጓሮ አትክልት ስራን ለመተግበር ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች

በመኖርያ ግቢ ውስጥ ለሚደረጉ የጓሮ አትክልት ስራዎች ላይ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው።

### 4.2.1 ምቹ ሁኔታዎች

በመኖርያ ግቢ ውስጥ ለሚደረጉ የጓሮ አትክልት ስራዎች ላይ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች በጥቂቱ፡-

- በማህበራትና በግለሰብ ደረጃ በቂ የሆነ የግብዓት አቅርቦት በከተማው አካባቢው መገኘቱ፤
- የጓሮ አትክልት ልማት ለመተግበር የሚያስችሉ በቂ፣ አዋጭ እና አማራጭ መንገዶች መኖራቸው፤
- የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳት ልማት ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ለመስራት የሚያስችል ተስማሚ የአየር ሁኔታ መኖሩ፤
- ማህበረሰቡ የግብርና ውጤቶችን የመግዛት ፍላጎቱ ከግዜ ወደ ግዜ መጨመሩ፤

- የህበረተሰቡን ፍላጎት የሚመጥኑ የምርት አቅርቦት እና ፍላጎት መኖሩ፤
- በአነስተኛ ወጪ እንዲሁም በተገደበ የመሬት ይዞታ መተግበር የሚቻል መሆኑ፤ እንደ ምቹ ሁኔታ የሚታዩ ናቸው፡፡

### 4.2.2 ተግዳሮቶች

በመኖሪያ ግቢ ውስጥ ለሚደረጉ የጓሮ አትክልት ስራዎች ላይ የሚያጋጥሙ መሰናክሎች በጥቂቱ፡-

- በየከተማው ያሉ ብዙ ተከራዮች በተከራዩበት ቤት የሚገኝ ግቢ የጓሮ አትክልት ለማምረት አለመፍቀድ፤
- ቆጣቢ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ባህል በህብረተሰቡ አለመስረፁ፡
- አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት ለምሳሌ ውሀ፣ የተባይ/ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ እንዲሁም የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉ አሰራሮችን በሚገባ አለመሰራቱ፤
- በግለሰቦች እንዲሁም በወጣት ማህበራት የተመረቱ ምርቶች ለስርቆት ተጋላጭ መሆን
- በዘርፉ ላይ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል የአቅም ግንባታ ስልጠና የሚሰጡ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በበቂ ደረጃ አለመኖራቸው፤
- ከመኖሪያ ቤቶች፤ ከወንዞች እና ፋብሪካዎች በሚወጡ መርዛማ ተረፈ ምርቶች በከተማ ግብርና ስራው ላይ ተፅዕኖ ማሳረፋቸው፤
- አምራቾች በዘርፉ ላይ ያላቸው እውቀት አነስተኛ መሆን እና የባለሙያ እገዛ አለማግኘት፤
- ለከተማ ግብርና የሚያስፈልጉ ማለትም የመሬት/መስሪያ ቦታ፣ ውሃ እንዲሁም ከውጭ ሀገር በምንዛሪ ተገዝተው የሚመጡ አስፈላጊ ግብዓቶች እጥረት መኖር፤

# 5. የከተማ ግብርናውን ስራ የተከተለው አካሄድ

የአንድ ፕሮጀክት ስኬታማነት የሚመዘነው የታቀዱ ስራዎች ተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር በተገቢው መንገድ እንዲደርስ የማስቻል ሂደት ሲኖር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ፔለም ኢትዮጵያ በተለያዩ የፕሮጀክት አካባቢዎች የሚተገበሩ ስራዎች ዘላቂነታቸው የሚረጋገጠው ተጠቃሚው ማህበረሰብ ከገደብ የለሽ የግብዓት ጠባቂነት አስተሳሰብ የፀዳ ሲሆን ነው የሚል እምነት አለው፡፡

ስለሆነም ፔለም ኢትዮጵያ በከፊል አርብቶ አደር፣ አርሶአደር ማህበረሰብ እንዲሁም በከተሞች ላይ የሚተገብራቸው ስነ-ምህዳራዊ የግብርና ስራዎች የአካባቢው መስተዳርርና ማህበረሰብ በባለቤትነት መንፈስ ራሱ እንዲያስቀጥላቸው ለማድረግ የሚያስችሉ እንዲሁም እንደ አሰራር የሚከተላቸው ተፅእኖ ፈጣሪ በጎ አሰራሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች በአካባቢው ከሚገኙ የግብርና ባለሞያዎች ጋር እኩል የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ተጠቃሚዎቹ ትክክለኛ የአሰራር ቴክኒካዊ መረጃዎች ወይም ክህሎቶች እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡
- የንድፈ-ሀሳብ /theorethical) ስልጠና ለተጠቃሚዎች እምብዛም ጠቃሚ ባለመሆኑ የሚዘጋጁ ስልጠናዎች አሳታፊ፣ በተግባር የተደገፉ ወይም ተጠቃሚዎች በአይናቸው አይተው ሊማሩባቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
- ማንኛውም የፕሮጀክት ስራ በሚቀረፅበት ወቅት ጠባቂነትን በሚያመጣ መልኩ መሆን የለበትም፡፡ ተጠቃሚዎች መሬት ላይ መከወን በሚጠበቅባቸው ስራ ላይ ትኩርት ማድረግ አለባቸው እንጂ የሚያገኙትን ጥቅም ወይም አበል ማሳደድ ላይ ትኩረት ማድረግ የለባቸውም፡፡

# 6. የተገኙ ውጤታማ ስራዎች

## 6.1. መግቢያ

ፔለም ኢትዮጵያ ከብሬድ ፎር ዘወርልድ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት በአባል ድረጅቱ ማለትም በምርጥ ተሞክሮ ማህበር በኩል ስነ-ምህዳሩን የጠበቀ የከተማ ግብርና ስራ በአዲስ አበባ መስተዳደር የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ላይ ተፈጥሯዊ ግብዓቶችን በመጠቀም የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ስራ እንዲሁም በእንስሳት ህክምና ድጋፍ ዙርያ ላይ ትኩረት በማድረግ ላለፉት ሁለት አመታት የተሳካ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የፕሮጀክቱ ዋና ዋና አላማዎች፡-

- ከአካባቢው ስነ-ምህዳር ጋር ተስማሚ የሆኑና ምርትና ምርታማነትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ አሰራሮችን ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች፣ ለግብርና ባለሞያዎች፣ እና አጋር ድርጅቶች በተግባር የታገዘ ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በወረዳው የሚገኙ ተጠቃሚዎች በግቢያቸው ውስጥ ለአሰራር በሚያመች መልኩ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬን በማምረት፣ ጤናማ ምግብ እንዲመገቡ እንዲሁም ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ በማስቻል፤ የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ፣
- ከተለያዩ የልማት አጋር አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት እና ዘላቂ የስራ አጋርነት መፍጠር፡፡

የፕሮጀክቱ አጀማመር በቅድሚያ ለፕሮጀክቱ መሳካት አስተዋፅኦ ያደረጉና መሰረት የጣሉ ሂደቶችን አስቀምጦ ስራውን ጀምሯል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ በአዲስ አበባ መስተዳደር የከተማ ግብርና እና አርሶአደር ልማት ኮሚሽን ጋር ምክክር ተደረገ፡፡ እሱም፡- ስለ ፕሮጀክቱ ዓላማ፣ ስለታቀዱ ስራዎች፣ እንዲሁም ፕሮጀክቱ በወረዳውና በምርጥ ተሞክሮ ማህበር አማካኝነት እንደሚከናወን በቂ ማብራርያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በመቀጠል የኮሚሽኑ ባለሞያዎች የታቀደው የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ስራ ለከተማው የማህበረሰብ ክፍል እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑና ድርጅቶቹ

የልማት አጋር መሆናቸውን በማመስገን በተመረጠው ወረዳ ለሚተገበሩ የልማት ስራዎች ተፈፃሚነት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር እንደሚያደርጉ፤ የሚሰጠውም በተግባር የታገዘ ሙያዊ ድጋፍ የወረዳውን ባለሞያዎች አቅም ከፍ እንደሚያደርግና የእውቀት ሽግግር እንደሚፈጥር ሙሉ ተስፋ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን በሂደት የሚያጋጥሙ ለማናቸውም እንቅፋቶች መፍትሄ ለማበጀት አብረው እንደሚሰሩ ፍቃደኝነታቸውን በመግለፅ ስራው በፍጥነት እንዲጀመር ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡

ከምክክሩ በኋላ ከየካ ክ/ከተማ የከተማ ግብርናና አርሶአደር ልማት ፅ/ቤት ሃላፊ ጋር በመገናኘት ውይይት ከተደረገ በኃላ የፕሮጀክቱ ተግባሪ ድርጅት በፈለገው ወረዳ ውስጥ ገብቶ መስራት እንደሚችል መልካም ፍቃዳቸው መሆኑንም ገለፁ፡፡ በመጨረሻም የፕሮጀክት ስራው በሚከናወንበት ቦታ ማለትም የካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የከተማ ግብርናና አርሶአደር ልማት ፅ/ቤት ሃላፊዎች እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለሞያዎች ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር ተወካዮች ጋር በጋራ በመሆን የፕሮጀክቱ እቅድና ዓላማ፤ እንዴት መተግበር እንዳለበት፣ የተጠቃሚዎች መረጣን በተመለከተ፤ በተደጋጋሚ በመገናኘት ጥልቅና ገንቢ ውይይቶች የተደረጉ ሲሆን በመቀጠል ለፕሮጀክት ትግበራና ክትትል አመቺነት ሲባል የመግባቢያ ሰነድ እንዲዘጋጅ ስምምነት ላይ ተደርሶ ስራው ተጀመረ፡፡

## 6.2. የተሰጡ ስልጠናዎች

ስራውን ለመጀመር የከተማው ግብርና እና አርሶአደር ልማት ኮሚሽን ድጋፍ ለማድረግ ቃል በገቡልን መሰረት በከተማ ግብርና ውጤታማ የሆኑ፣ የተሻለ ስራ የሰሩ እና ለማስተማሪያነት መሆን የሚችሉ የተሰሩ ሰራዎች የሚገኙበት ክፍለ ከተማ እንዲጠቁሙን እንዲሁም አስፈላጊውን ትብብር እንዲደረግልን ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት ኮልፌ ቀራንዮ የተሻለ ተሞክሮ እንዳለ ነግረውን የምንፈልገውን እገዛ ከሚያደርግልን ሰው ጋር አገናኙን፡፡

ይህም በመሆኑ ክፍለ ከተማው ባደረግልን ቀና ትብብር በቅድሚያ የተባሉትን ቦታዎች ሄደን ጎበኘን፡፡ የጎበኘናቸው ቦታዎች ሁሉንም

ያማከሉ ማለትም በሰፊ ቦታ፣ በአነስተኛ ቦታ፣ በከፍታ እንዲሁም በእቃ ላይ የተሰሩትን ለማስተማሪያነት እንደሚጠቅሙን ለይተን ተመለስን፡፡ እንግዲህ ሂደቱ በዚህ መልኩ ግልፅ ከተደረገ በኃላ ነበር ወደ ፕሮጀክት ትግበራ የተገባው፡፡

### 6.2.1. ለባለሞያዎች የተሰጠ ስልጠና

በመጀመሪያ ለመስራት የታሰበው በፅህፈት ቤቱ ያሉትን ባለሙያዎች የታቀደውን ስራ በተሻለ መንገድ ለመስራት ያስችላቸው ዘንድ እንዲሁም እንዴት እንደሚተገብሩት ግልፅ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ተብሎ የተዘጋጀ ነበር፡፡ ተግባር ተኮር ስልጠናው ከልምድ ልውውጡ ጋር በማቀናጀት ለሁለት ቀን ተዘጋጀ፡፡ የስልጠናው ዋና አላማም የታቀደው ስራ በተሳለጠ መልኩ እንዲከናወን ለማስቻል፣ ባለሞያዎቹ የነበራቸውን እውቀት በማሳደግ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ እንዲሁም የስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸውና አመርቂ ስራ እንዲሰሩ ለማድረግ የታቀደ ነበር፡፡

ስልጠናው ላይ በተወሰነ መልኩ የንድፈ ሀሳብ ገለፃ የነበረ ሲሆን ትኩረት በተደረገባቸው ነጥቦች ማለትም፤ የከተማ ግብርና ምን ማለት እንደሆነ፣ አስፈላጊነቱና የሚሰጠው ጥቅም፣ ለመተግበር ያለው ምቹ ሁኔታና ተግዳሮት፣ የአተገባበር አይነቶች እንዲሁም በምርት አመራረት ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ላይ የተሻለ ሃሳብ እንዲንሸራሸርና ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲሁም እውቀት እንዲያዳብሩ አድርጓል፡፡

በስልጠናው ወቅት የተማሪና የአስተማሪ አይነት ሳይሆን ሁሉም የሚማማርበት፣ በየርዕሶቹ ላይ የተደረጉት የቡድን ውይይቶችም ሁሉም ተሳታፊዎች በነፃነት ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚያስችላቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም በውይይቱ ወቅት ከዚህ በፊት ተግዳሮት ሆነውባቸው የነበሩ ነገሮችን በግልፅ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያስቀመጠ በመሆኑ በሚተገበሩት ስራዎች ላይ ለሚያጋጥሙ ተመሳሳይ እንቅፋቶች ከወዲሁ እርምት ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ስልጠናው ተካሂዶል፡፡



ምስል 1፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች በተሰጠው ስልጠና ላይ የቡድን ውይይት ሲያደርጉ

### 6.2.2. የመስክ ጉብኝት

የመስክ ጉብኝትና ተግባር ተኮር ስልጠናን እንደ መርህ አድረጎ የተሻለ ግንዛቤን እና ተነሳሽነትን መፍጠር እንደሚቻል በማመን ነበር የመስክ ጉብኝቱ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ 2 አስቀድመው በተመረጡ ቦታዎች ላይ ነው የተደረገው፡፡ በዚህም ወቅት አስተማሪ ናቸው ተብለው የታሰቡት ቦታዎች ሁሉ በጉብኝቱ የተሸፈኑ ሲሆን በተለይ ደግሞ የተለያዩ ያገለገሉ እቃዎችን በመጠቀም እንዲሁም የከፍታ የአመራረት ዘዴ የተሳታፊዎቹን ቀልብ በእጅጉ የሳቡ ነበሩ፡፡

ተሳታፊዎቹም ያዩትን ነገር ለፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ለማሳየትና ለማስተግበር ተነሳሽነታቸው በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ጉብኝቱ የታሰበለትን አላማ ያሳካ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት ነበር ባለሞያዎች አቅማቸውን የሚገነቡበት የመጀመርያው የክልስ-ሃሳብና የመስክ ጉብኝት በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀው፡፡



ምስል 2፡ የባለሙያዎች የመስክ ጉብኝት (ልምድ ልውውጥ)



ምስል 3፡ ስልጠናና የልምድ ልውውጥ





ምስል 4፡ ስልጠናና የልምድ ልውውጥ

### 6.2.3. የተጠቃሚዎች መረጣ

በፕሮጀክቱ በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረጉት ተሳታፊዎች የተለዩት በወረዳው የከተማ ግብርና እና አርሶአደር ልማት ፅህፈት ቤት አማካይነት ነበር፡፡ የወረዳው ባለሙያዎች ስልጠናው ላይ ያዩትን ነገሮች መሰረት በማድረግ በሶስት መንደር (ክላስተር) ማለትም በምዕራብ፣ በምስራቅ እና በማዕከላዊ በማድረግ ከፋፍለው ለዩዋቸው፡፡

የወረዳው ባለሞያዎች ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን የመረጡት የመስራት ፍላጎቱ ያላቸው፤ በአነስተኛ የግብዓት ድጋፍ መስራት የሚችሉ ወይም ብዙ የማይጠብቁ፤ የሚሰጣቸው ሙያዊ ድጋፍ ተግባር ላይ ለማዋል ቁርጠኝነቱ ያላቸው፤ ማናቸውም የማህበረሰብ ክፍል (አባዎራዎች፣ እማወራዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች ወዘተ) መሳተፍ ይችላሉ በሚሉና ተያያዥ መመዘኛዎችን መሰረት በማድረግ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት የተጠቃሚዎች መረጣ ተከናውኖ ሙሉ መረጃ በወቅቱ ለምርጥ ተሞክሮ ማህበር ተላልፏል፡፡

## 6.2.4. የተጠቃሚዎች ስልጠና

ለወረዳው የከተማ ግብርናና አርሶአደርልማት ፅ/ቤት ለባለሙያዎች እንደተደረገው ሁሉ ለተጠቃሚዎችም የንድፈ ሃሳብ ስልጠና እና የመስክ ጉብኝት ተካሂዷል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በግለሰብ ደረጃ እንዲሁም በክፍለ ከተማ ደረጃ የተሰሩ የተለያዩ አስተማሪ ስራዎችን ተጎብኝቷል፡፡ በተጨማሪም በወረዳው አካባቢ በሚገኝ በልማት ኮሚሽኑ የሚተዳደር የከተማ ግብርና ሰርቶ ማሳያ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተሰሩ ጥቃቅን ጅማሬዎች እንዲሁም በታዳጊ የተሰራ የተሳቦ ቀልዝ (ቨርሚ ኮምፖስት) የማዳበሪያ አዘገጃጀት ዓይነት ለመጎብኘት እድሉን አግኝተዋል፡፡ በጉብኝታቸው ወቅትም ለነበሯቸው ጥያቄዎች ከአስጎብኚዎች እንዲሁም ከተግባሪዎች በቂ የሆነ ማብራሪያ እና ምላሽ አግኝቷል፡፡



ምስል 5፡ የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ስልጠና

በከተማ ግብርና ሰርቶ ማሳያው ጉብኝት ወቅት ከመሬት ዝግጅት አንስቶ፣ ችግኝ አፈላልን እና ማዛመትን በተመለከተ፤ ከተዛመተም በኋላ መሰራት ስላለባቸው ስራዎች ምርቱ ደርሶ እስከሚነሳ ድረስ ያለውን ሂደት ምን ይመስላል በሚል በስፋት በአይናቸው መመልከታቸው እንዲሁም በኮልፌ ቀራኒዮ ጉብኝታቸው ወቅት በእድሜ የገፉ ሰዎች የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን በግቢያቸው ውስጥ እያመረቱ ቤተሰባቸውን እየመገቡ ከዚያም አልፈው እንደ ገቢ ምንጭ መጠቀም መቻላቸው ከፍተኛ የሆነ

የስራ ተነሳሽነትን እንዲሁም መንፈሳዊ ቅናት እንዲያድርባቸው አድርጓል፡፡



ምስል 6፡ የተጠቃሚዎች የመስክ ጉብኝት (የልምድ ልውውጥ)

ከዚህ በተለየ ደግሞ ከዚህ በፊት ፈፅሞ የማያውቁት ማለትም ትሎችን በመጠቀም የሚዘጋጅ የማዳበርያ አይነት ወይም የተሳቦ ቀልዝ (ቨርሚ ኮምፖስት) አመራረት ዘዴ ማየት መቻላቸው በጣም አስደስቷቸዋል፡፡ የተለያዩ የኩሽና ቆሻሻዎች (የአትክልትና ፍራፍሬ ልጣጮችና የቤት ጥራጊ) እንደ ግብአት በመጠቀም ከፍተኛ የሆነ ንጥረ-ነገር ያለውን ማዳበሪያ ማምረትና የአፈር ለምነትን መጨመር፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ብሎም የአካባቢ ብክለትን መቀነስ በመቻሉ በጣም ነበር ያስገረማቸው፡፡

የተሳቦ ቀልዙን ያዘጋጀው ታዳጊ በእምነት ሃይሉ እንዴት እንደሚሰራ ለሰልጣኞች በሚገባ ነበር ያስረዳቸው ከዚያም አልፎ በራሱ ተነሳሽነት መሞከር ለሚፈልጉ የተሳቦ ቀልዝ (ቨርሚ ኮምፖስት) ለማዘጋጀት የሚጠቅመውን ትል በስጦታ መልክ ሰጥቷቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በንድፈ-ሃሳብ ስልጠናውም ሆነ በመስክ ጉብኝቱ ላይ የተሳታፊዎች ንቁና ከፍተኛ ተሳትፎ በመኖሩ ጥሩ የሆነ የሃሳብ መንሸራሸር በመኖሩ ስለ ከተማ ግብርና የተሻለ ግንዛቤ እንዲፈጠር እንዲሁም አይናቸው እንዲገለጥ መንገድ ከፍቷል፡፡



ምስል 7፡ ወጣት በእምነት ሃይሉ የሰራው የቨርሚ ኮምፖስት ርብራብ ለህፃናት እና ወጣቶች ሲያስጎበኝ

## 6.2.5. የግብአት አቅርቦት

በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተመረጡት ተጠቃሚዎች ከዚህ በፊት በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን የጓሮ አትክልት በግቢያቸው የጀመሩ በመሆናቸው የተሰጣቸው ስልጠና የነበራቸውን ውስን እውቀትና ተሞክሮ ይበልጥ ለማጎልበት እንዲሁም ከበፊቱ በተሻለ አሰራርና ሰፋ ባለ መልኩ በማምረት ሂደቱ ይበልጥ ለመሳተፍ የመስራት ተነሳሽነታቸውን ጨምሮላቸዋል፡፡

ስልጠናውን ተከትሎ የተለያዩ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንደ የአትክልት ዘር (የሀበሻ እና ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ቀይስር፣ ካሮት፣ ስላጣና ቆስጣ)፣ የፍራፍሬ ችግኝ (ካዝሚርና አፕል) የውሃ ማጠጫ ጀሪካን እና ጎማ፣ መኮትኮቻ እንዲሁም ለመድሃኒት መርጫ የሚሆኑ አነስተኛ ፕላስቲኮች የስራ አፈፃፀማቸው እየታየ በሂደት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለእንስሳት ህክምና የሚውሉ የተለያዩ የህክምና እቃዎች ማለትም የተለያዩ መድሃኒቶች፣ ለቀዶ ጥገናና ክትባት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ግዢ ተከናውኖ በወረዳው የእንስሳት ህክምና ዘርፍ ክፍል አማካኝነት ለማህበረሰቡ እንዲዳረስ ተደርጓል፡፡

## 6.2.6. ለታዳጊዎች የተሰጠ ሥልጠና

እንደሚታወቀው በሀገራችን የኮቪድ-19 መከሰት ብዙ ነገሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ የእንቅስቃሴ መገደብ፣ የትምህርት ቤቶችና የመስሪያ ቤቶች መዘጋት ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ እገዳዎች ማህበረሰቡ በቤት ውስጥ እንዲቆይ በማስገደዳቸው አብዛኛው ህብረተሰብ ለድባቴ ተጋላጭ እንዲሆን መንገድ ከፍቷል፡፡ በተለይም ደግሞ ልጆች ትምህርት ቤት መሄድ ባለመቻላቸው ያላቸውን ውድ ግዜያቸውን ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ጠቃሚ ባልሆኑ ጉዳዮች እንዲያሳልፉ ምክንያት በመሆኑ ከራሳቸው አልፎ ለወላጆቻቸው ከፍተኛ ጭንቀትን ፈጥሯል፡፡

ፕሮጅክቱም ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተወሰነ መልኩ ልጆችን አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ ለመታደግ እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውን ባላቸው አቅም ሁሉ ለመርዳት እንዲችሉ በፕሮጅክቱ ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች እድሜያቸው ከሰባት አመት በላይ ለሆኑ ልጆች እንዲሁም በፕሮጀክቱ ያልታቀፉ ቤተሰቦች ልጆችን በመቀላቀል የጓሮ አትክልት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ለምን እንደሚተከል፣ እንዴት እንደሚተከል፣ የጓሮ አትክልቶችን መመገብ የሚያስገኙት የጤና ጥቅሞች፣ ከተከልን በኋላ መደረግ ስላለባቸው የእንክብካቤ ስራዎች አስመልክቶ በተግባር የተደገፈ የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡



ምስል 8፡ የወጣቶች ተሳትፎ

ተሳታፊ የነበሩት ልጆችም አብዛኛውን ነገሮች ከትምህርታቸው ጋር የተያያዘ በመሆኑ በጣም የነቃ ተሳተፎ በማድረግ ስልጠናውን በመከታተል የነበራቸውን ግንዛቤ ማስፋት ችለዋል፡፡ በስልጠናው ወቅት የአብዛኛዎቹ ልጆች ወላጆች በስልጠናው ላይ በአካል የተገኙ ሲሆን የስልጠናው ተሳታፊ ታዳጊ ልጆች ስልጠናውን ከወሰዱባት ቀን ጀምሮ የጥናት ግዚያቸውን በማይሻማ መልኩ ቀለል ቀለል ያሉ ስራዎች ላይ በመሳተፍ ቤተሰቦቻቸውን ለማገዝ ቃል ገብተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

## 6.2.7. የአፈር ለምነትንና የእፅዋት ጥበቃን አስመልክቶ የተሰጠ ስልጠና

አስፈላጊ የሆኑ የአትክልት ዘሮች ለሁሉም ተጠቃሚዎች ከተከፋፈሉ በኋላ ምርትና ምርታማነትን ተፈጥሮዓዊ በሆነ መንገድ ለማሳደግ ስነ-ምህዳሩን በማይጎዱና በአካባቢው በሚገኙ ግብዓቶች መዘጋጀት የሚችሉ የአፈር ለምነትን ማበልፀጊያ አሰራሮች እንዲሁም ለተባይና በሽታ ጥቃት እንደ ቅድመ መከላከያ የሚረዱ ውህዶች አዘገጃጀት በተመለከተ ተግባር ተኮር ስልጠና በአንድ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተካሂዷል፡፡

የተደረጉት ተግባራዊ ስልጠናዎችም የቨርሚ ኮምፖስት፣ ከአመድ፣ ዘይት እና ሳሙና የሚሰራ (ash brew) አዘገጃጀት የሚመለከት ነበር፡፡ የቨርሚ

ኮምፖስት አስመልክቶ በተደራጀ መልኩ ኮምፖስቱን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉት ግብዓቶች ማለትም የተሳቦ ትል ማቅረብ፣ በቀላሉ የሚበሰብሱ እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ተረፈ ምርቶች ማሰባሰብ፣ አፈር እና ውሃ አቅርቦት ከሚሟላት አንስቶ የአሰራር ሂደቱን፣ አጠቃቀሙን፣ አያያዙን፣ የሚሰጠውን ጥቅም እንዲሁም የተባይ መከላከል በተመለከተ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ያለውን የአሰራር ሂደት በተመለከተ ሰልጣኞቹ እጃቸውን አስገብተው የተሳተፋበት ሙሉ በሙሉ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

## 6.2.8. የፍራፍሬ ችግኝ ማከፋፈል

ከተለያዩ የጓሮ አትክልት ዘሮች በተጨማሪ ጥቅሙ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚቋደሱት ለስነ-ምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የደጋ ፍራፍሬዎች ማለትም የዘይቱን፣ የካዝሚር፣ የአቮካዶ እና የአፕል ችግኞች ግዢ በመፈፀም በግቢያቸው ለመትከል የሚያመች ቦታ ላላቸው የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች እንዲከፋፈሉ ተደርጓል፡፡

## 6.2.9. ክትትልና ድጋፍ

በማምረት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ የደረሰበት ሁኔታ ምን ደረጃ ላይ ነው የሚለውን ለመገምገም ከአስርእስከ አስራ አምስት ቀናት በወሰደ ጊዜ አስፈላጊውን ክትትል እና ድጋፍ በምርጥ ተሞክሮ ማህበር ሰራተኞችና በወረዳው ባለሙያዎች አማካኝነት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፔለም ኢትዮጵያ ሰራተኞች ከምርጥ ተሞክሮ ማህበርና ከወረዳው ባለሞያዎች ጋር በጋራ በመሆን በየተጠቃሚው ቅጥር ግቢ በመዞር አስፈላጊ ሙያዊ ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መሰረት በሚፈለገው ደረጃ ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡

## 6.3. በወረዳው ላይ የከተማ ግብርና በመተግበሩ የተገኙ ውጤቶች

ይህን የጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች በማምረት ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ሂደት ውስጥ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም በአዲስ አበባ መስተዳደር የከተማ ግብርና እና የአርሶአደሮች ልማት ኮሚሽን፣ የየካ ክ/ከተማ የከተማ ግብርናና አርሶአደር ልማት ፅ/ቤት፣ ፔለም ኢትዮጵያ፣ ምርጥ ተሞክሮ ማህበር፣ በተለይ የወረዳ 10 የከተማ ግብርናና አርሶአደር ልማት ፅ/ቤት ባለሞያዎች እንዲሁም የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች የነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት ለተገኘው ፈጣን ስኬት የጎላ አስተዋፅዖ ነበራቸው። በመሆኑም ከላይ በተገለፁት ዝርዝር ስራዎች መሰረት በማድረግ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር መደረጉ ለሌሎች አስተማሪ የሆኑ፤ ስራው በሌሎች አካባቢዎች ቢተገበር ሊያመጣ የሚችለው በጎ ተፅእኖ በአጠቃላይ በታቀደው መሰረትና በተለዩት አላማዎች መሳካት ምክንያት የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላሉ የሚለው እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ሁሉም ተጠቃሚዎች በጓሮ አትክልት አመራረት ላይ የነበራቸውን ውስንነትና በተግባር ያልዳበረ እውቀት ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ችለዋል።
- በጣም በአጭር ግዜ ውስጥ በቀላል ወጪ ትኩስና ጤናማ የሆነ አትክልት አምርተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መመገብ ችለዋል፤ እንዲሁም ጎረቤቶቻቸውም የምርቶቻቸው ተቋዳሽ እንዲሆኑ አስችሏል።
- ቀላል በማይባሉ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ያመረቱት ምርት ለምግብነት ከመጠቀምም አልፈው ወደ ገበያ ወስደው በመሸጥ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በማስገኘት ኑሯቸውን ለማገዝ ችለዋል።
- ተጨማሪ የአትክልት ችግኞችን በማፍላት ለሌሎች ፈላጊዎች በመሸጥ በገቢው ራሳቸውን መጥቀም ችለዋል ማህበረሰቡን በከተማ ግብርና ስራ ላይ እንዲሳተፍ/እንዲሰማራ ምሳሌ መሆን ችለዋል።
- በአቅራቢያቸው በቀላሉ የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም ለእፅዋት ጤንነት መጠበቂያ ሊሆኑ የሚችሉ ተፈጥራዊ መድሃቶችን ማዘጋጀት ተችሏል። በዚህ መሰረትም የበቀሉ ተክሎቻቸው በተሻለ ሁኔታ

ከበሽታ ነፃ እንዲሆኑና ለኬሚካሎች ግዢ የሚወጣው ገንዘብ እንዲቀር አግዟቿል፡፡

- ሸርሚ ኮምፖስትን በማዘጋጀት የአፈርን ለምነት ጨምረዋል፤ ምርትና ምርታማነትን አሳድገዋል፤ የአካባቢ ብክለት የተሳቦ ቀልዝ በመተግበሩ በግቢ ውስጥ የሚከማቸውን የቆሻሻ መጠን ቀንሰዋል እንዲሁም በተጠቃሚዎች ግቢ ውስጥ ጤናማ አካባቢ ተፈጥሯል፡፡
- ልጆች ስለ ጓሮ አትክልት አመራረትና እንክብካቤ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡
- ልጆች ያላቸውን ትርፍ ሰዓት አልባሌ ቦታ ከማሰለፍ ይልቅ አትክልቶችን መንከባከብ እንዲችሉ የሚያደርግ ፍላጎት፣ የመስራት ክህሎት እንዲሁም ተነሳሽነት እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡
- ወላጆች የከተማ ግብርናን በተመለከተ ከልጆቻቸው ጋር ተጋግዘው የመስራት ባህልን የበለጠ ለማጎልበት የራሱን አስተዋፅዖ አበርክቷል፤ በተጠቃሚዎች መካከል እርስበርስ የመማማር ብሂልንም አሳድገዋል፡፡
- በተለይም ደግሞ ሴቶች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ቤተሰብን የመመገብ ሃላፊነታቸው ላይ የነበረባቸውን የጉልበትና የጊዜ ጫና በተወሰነ መልኩ እንዲቀንስላቸው አስችሏል፡፡
- የሴቶችና ወጣቶች በራስ የመተማመን ብቃት ተሻሽሏል፤ ከዘርፉ ቤተሰባቸውን መደጎም ጀምረዋል አጠቃላይ ተጠቃሚነታቸውን አሳድገዋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪም ከተጠቃሚዎች አልፎ በቀላሉ ወደ ማህበረሰቡ መድረስ በመቻሉ ተጠቃሚዎቹን በመመልከት በአካባቢው ላይ ያሉ ማህበረሰቦች በአብዛኛው የጓሮ አትክልቶችን ከጎረቤቶቻቸው ልምድ በመውሰድ ማምረት እና መጠቀም ጀምረዋል፤ በቀጣይ በፕሮጀክቱ ውስጥ በመታቀፍ አስፈላጊ ስልጠናዎችን ለማግኘት ፍላጎቱ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ ሲታይ የዚህ ፕሮጀክት በወረዳው መተግበር መቻሉ የከተማ አሰተዳደር የልማት ኮሚሽኑ እንደ መርህ ይዞት የተነሳውን ምግባችን ከደጃችን የሚለውን መርህ ለማሳካት አጋዥ የልማት አጋር ለመሆን ተችሏል፡፡

# 7. ስኬታማነት በከተማ ግብርና

## 7.1. መግቢያ

ላለፉት ከ20 በማይበልጡ የፕሮጀክት ወራት ምርጥ ተሞክሮ ማህበር ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የግብርና ዘርፍ ባለሞያዎች ጋር በመሆን በከተማ ግብርና የጓሮ አትክልት መስራት ለሚፈልጉ ከ40 በላይ ለሚሆኑ ተጠቃሚዎች አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ቀድሞ ከነበራቸው እውቀት፣ ልምድና ትግበራ ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ እንዲሉ የተቻለውን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፤ በአሁኑም ሰዓት ተገቢውንና አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ይህ ፕሮጀክት ዓላማው የምግብ እና የስነ-ምግብ ዋስትናን በማስጠበቅ፣ የገቢ ምንጭን በመፍጠር፣ በእውቀት በማጎልበት፣ ስራን በመፍጠር፣ ሞራላዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ በማድረግ፣ ከኬሚካል የፀዳ ተባይ መከላከያና ማዳበሪያ በማዘጋጀትና በመጠቀም፣ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማስዋል የአካባቢና የከተማን ፅዳትና ውበት በማስጠበቅ፣ የዘር፣ የችግኝና የግብርና ቁሳቁስ በማበርከት፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ተጠቃሚዎች አምርቶ ለራስ በመጠቀም፣ ሸጦ ገቢ በማግኘት፣ እውቀትን በማዳበርና ለሌሎች በማስተላለፍ፣ የስራ ፈጠራ (የተለያዩ አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ምርት ማግኘትን)፣ ጠንካራ ስብዕና፣ ከፍተኛ ሞራልና መነቃቃት በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ፕሮጀክቱ የሚተገበረው ከእማወራዎች (የቤት እመቤቶች)፣ ከአባወራዎች፣ ከወጣቶች (ወንድና ሴት)፣ ከታድጊ ተማሪዎች ጋር ሲሆን፤ ስራው በወቅቱ የነበሩትን ችግሮች በትንሹ ለመቅረፍ አግዟል።

እንደሚታወቀው ይህ ስራ የተጀመረው በሀገራችን ብሎም በዓለማችን ከፍተኛ የጤና ጉዳትና ሞት እያስከተለ ባለው የኮቪድ-19 በሽታ ወረርሺኝ ወቅት በመሆኑ ቀላል የማይባል እንቅስቃሴ በማድረግ ከታች የተጠቀሱትን ስኬታማና ውጤታማ የሆኑ ሰራዎችን ለመስራት ተችሏል።

በከተማ ግብርና ፕሮጀክት ውስጥ የተደረጉ ስኬታማ እና ውጤታማ የምርጥ ተሞክሮ ማህበር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የጓሮ አትክልት ምርት (ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ የሀበሻ ጎመን፣ ጥቅል ጎመን፣ ቀይስር፣ ካሮት፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲምና ቃሪያ)፡፡
2. ከአካባቢ የሚገኝ ቆሻሻ ቨርሚ ኮምፖስት ማምረትና መጠቀም መቻል፡፡
3. ምርጥና የተዳቀለ የፍራፍሬ ችግኝ (አቮካዶ፣ አፕል፣ ካዝሚርና ዘይቱን) አመራረት፡፡
4. ከኬሚካል የፀዳ፣ የተባይ መከላከያ (ፀረ-ተባይ) መስራትና ጥቅም ላይ ማዋል መቻል ናቸው፡፡

## 7.2 ምሳሌዎች

በእነዚህ ተግባራት ምክንያት የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ያስገኙት ውጤትና ጥቅም፡-

### 7.2.1. ከእማወራዎች ጋር የተደረገ የማነቃቂያ ስራና ያስገኘው ውጤት

እንደሚታወቀው በአገራችን ቀደም ብሎም በነበረው አሁንም ድረስ ባለው ሁኔታ አብዛኛዎቹ ባለትዳር እንስቶች ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በቤት ውስጥ ሆነው ቤተሰብን በመምራት እና በመንከባከብ በመሆኑ ለተለያዩ የአዕምሮ ጭንቀትና ድባቴ ተጋላጭ ሲሆኑ ይስተዋላል፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ በወቅቱ ከተከሰተው የኮቪድ- 19 በሽታ ካስከተላቸው ማህበራዊ መስተጋብሮች ጋር ሲደመር ቀውሱን ከፍ ያደርገዋል፡፡

ይህ ፕሮጀክት እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በከፍተኛ ሁኔት በመንቀሳቀስ የተመረጡ ተጠቃሚዎች እንደዚህ ካለ ማህበራዊ ቀውስ እራሳቸውን የሚያላቅቁበትን የተለያዩ ስልጠናዎችን በጓሮ አትክልቶች፣ ከኬሚካል የፀዳ ተባይ እና በሽታ መከላከያ (ፀረ-ተባይ)ና ቨርሚ ኮምፖስት ስልጠና በመስጠት የስራ መነቃቃትና ፈጠራን የሚያጎለብቱበትን መንገድ ከፍቶ በማመቻቸትና በማሰራት ጉልህ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ለዚህም ውጤት ማሳያ የሚሆኑ ሁለት ተጠቃሚዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**ወ/ሮ መሰረት ዘውዴ፡-**

ወ/ሮ መሰረት ባለትዳር፣ የቤት እመቤትና የሁለት ታዳጊ ሴት ልጆች እናት ስትሆን፤ በነበረባት የትዳር ችግር ምክንያት እራስዋንም ሆነ ልጆችዋን የምታስተዳድረው ሰው ቤት ልብስ በማጠብ እና ከሴፍቲ ኔት በምታገኘው የድጎማ ገንዘብ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የኮቪድ- 19 በሽታ መከሰት እነዚህን የገቢ ምንጮች አስቀርቶባት ስለነበር ከባድ የሚባል ችግርና ጊዜ ላይ ነበረች፡፡

ይህች ሴት የምትኖረው በምትሰራበት ጠባብ ግቢ ውስጥ ቢሆንም ልጆችዋና መሬቱ ግን ያም እንዲያድሩ አልፈቀደችም፤ ያላትን ሞራልና አቅም አሰባስባ ከወረዳው ፅ/ቤት የጓሮ አትክልት ዘር በመውሰድ የተወሰኑ ምርቶችን እያመረተች መመገብ ቻለች፡፡ ይህ በእንዲህ እያለም ግን ችግሮችዋን በበቂ ሁኔታ መቅረፍ አለመቻልዋና የነበራትን የስራ ሞራልና ተነሳሽነት በእጅጉ በተዳከመ ሰዓት ላይ ነበር ከድርጅታችን ጋር የተገናኘችው፡፡



ምስል 9፡ የወ/ሮ መሰረት የጓሮ አትክልት

በተደረገላት የእውቀት (የስልጠና)፣ የተለያየ አይነት የጓሮ አትክልት ዘሮች፣ የግብርና ቁሳቁስና የእለት ተዕለት ክትትልና ድጋፍ አሁን ላይ በከፍተኛ ስራና ውጤት ላይ ትገኛለች፡፡ ዛሬ ላይ በዚህ ስራ አማካኝነት ቤተሰቧን መመገብና የምግብ ዋስትናን ማስጠበቅ ከመቻሏ በተጨማሪ ዋና የገቢ ምንጯ በማድረግ የሴቶች ቁጠባን በመክፈት ገንዘብ መቆጠብና ራሷን በራሷ ማስተዳደር በመቻሏ ከጥገኝነት በተወሰነ መላቀቅ ችላለች፡፡ ወ/ሮ መሰረት እንደምትለው የመጨረሻ ተስፋ ቆርጬ ወደ ከፋ ነገር ውስጥ ልገባ በነበርኩበት ሰዓት በተሰጠኝ ስልጠናና ድጋፍ ዛሬ ላይ ከባለቤቴም ሆነ ከጎረቤቶቼ ድጋፍ ተላቅቄ ራሴንም ሆነ ልጆቼን ለማስተዳደር በቅቻለሁኝ ትላለች፡፡

<u>ወ/ሮ በለጡ ጣሰው</u>፡-

ወ/ሮ በለጡ የቤት እመቤትና የሁለት ወጣት ልጆች እናት ስትሆን፤ አስቀድማ በዘርፉ ለረጅም አመት በግሏ የሰራችና ጥቅም ያገኘች ብትሆንም ውስጥዋ ያስብና ሊሰራ ይፈልግ በነበረው ልክ እንዳልሰራች ዘወትር ታስብና የተሻለ ልትሰራ ትሻ ነበር፤ ሆኖም ግን አጠገብዋ ሆኖ የሚያበረታታትና የሚደግፋት ባለመኖሩ ይህ ፍላጎት እንደተዳፈነ ቆይቶ

ነበር፡፡ በወቅቱ በተደረገላት ስልጠና፣ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት፣ ክትትልና ድጋፍ አማካኝነት በፊት ከነበራት የተሻለ መሰረታዊ የጓሮ አትክልት እውቀት፣ አሰራርና አተገባበር፣ የራስ እውቀትንና ፈጠራን በተለያየ መንገድ ማሳደግና ማጎልበት ችላለች፡፡



ምስል 10፡ የወ/ሮ በለጡ ጣሰው የጓሮ አትክልት በከፊል

ወ/ሮ በለጡ በከፍተኛ ደረጃ የስራ ፈጠራና የአዕምሮ መነቃቃት መፍጠር በመቻሏ፣ በተሻለ ጥራትና ብዛት የጎሮ አትክልትን እያመረተች ቤተሰቧ መመገብና የምግብ ዋስትናን ማስጠበቅ ከመቻሏ በተጨማሪ የገቢ ምንጭ በማግኘት የሴቶች ቁጠባን በመክፈት ገንዘብ መቆጠብና ራሷን በራሷ ማስተዳደር በመቻሏ ከጥገኝነት በተወሰነ መላቀቅ ችላለች፡፡

የአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም የከተማ ፅዳትና ውበትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለውን የቨርሚ ኮምፖስት (ብስባሽ) የአትክልት ማዳበሪያን ከሌሎች እማወራ ተጠቃሚዎች በብቸኝነት ጥሩ የሚባል የቨርሚ- ኮምፖስት ምርትን በማምረት፣ ለራስ በመጠቀምና ለሌሎች እውቀትን ከማስተላለፍ ባለፈ የምርቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በማስቻል ፈር ቀዳጅ መሆን ችላለች፡፡

### 7.2.2 ከአባወራዎች ጋር የተደረገ የማነቃቂያ ስራና ያስገኘው ውጤት

በአብላጫው የዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ሴቶችና ወጣቶች ቢሆኑም የተወሰኑ በትርፍ ሰዓታቸው የጓሮ አትክልትን መትከልና መንከባከብ ልዩ ደስታ የሚሰጣቸውና በስራው አማካኝነት የሚያደርጉትን የአካል እንቅስቃሴና የሰውነት መፍታታት የሚወዱ በከፍተኛ ደረጃ እንዳሉ በነበረው የልምድ ልውውጥ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በተጨማሪም በተደረገላቸው ድጋፍ የስራ ፈጠራና የአዕምሮ መነቃቃት በማምጣት፣ ከኬሚካል የፀዳ ተባይ/በሽታ መከላከያ (ፀረ-ተባይ) በመጠቀም በተሻለ ጥራትና ብዛት የጓሮ አትክልትን በማምረት የቤተሰብ አባላት መመገብ፣ የምግብ ዋስትናን ማስጠበቅና መንቀሳቀሻ የሚሆን የኪስ ገንዘብ ማግኘት ችለዋል፡፡

### 7.2.3 ከወጣቶች ጋር የተደረገ የማነቃቂያ ስራና ያስገኘው ውጤት

በሀገራችን ብሎም በአለማችን ስራ አጥነት እየተበራከተና ቁጥሩም ከፍ እያለ መምጣቱ የብዙዎችን የተማሩና ያልተማሩ ህብረተሰብ ጭንቀት መሆን ከጀመረ በርካታ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የኮቪድ-19 በሽታ በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋትና መሰራጨትን ተከትሎ በመጣው የስራ ማጣትና ስራ ፈትነት ቁጥር መጨመር ምክንያት እራሳቸውን መደበቂያና ጊዜ ማሳለፊያ ፍለጋ አላስፈላጊ ቦታ የሚውሉና አላስፈላጊ ስራ የሚሰሩ ወጣቶችን ማየት ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ የተስተዋለበት ነበር፡፡ ታዲያ ከዚህ በተቃራኒ እራሳቸውን በስራ በመጥመድ፣ የስራ ፈጠራ በማጎልበት፣ ከፍተኛ ሞራልና መነቃቃትን በመፍጠር ለቤተሰብና ለአካባቢው ህብረተሰብ እውቀትን ማጋራትና መደገፍ የሚችሉ ብርቱ ስራ ወዳድ ዜጋን ለመፍጠር ፕሮጀክቱ ቀላል የማይባል ድጋፍና ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**ወ/ሪት ገነት በቀለ፡-**

ወ/ሪት ገነት ወጣትና ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ወላጆችዋን የማስተዳደር ሀላፊነት ያለባት፣ ሀላፊነትዋን ደግሞ በብቃት እየተወጣች የምትገኝ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወጣት ሴት ነች፡፡ ቤተሰቦቿ ሰፊ መሬት ያላቸውና በግብርና የሚተዳደሩ ቢሆንም በጓሮ አትክልት ዙሪያ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ግን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከፕሮጀክቱ ጋር ከተገናኘችበት ዕለት አንስቶ በተደረገላት የስልጠና፣ የልምድ ልውውጥና ጉብኝት፣ የጎሮ አትክልት ዘሮች፣ የግብርና ቁሳቁስና የእለት ተዕለት ክትትልና ድጋፍ ዛሬ ላይ በከፍተኛ ስራና ውጤት ላይ ልትገኝ ችላለች፡፡



ምስል 11፡ የወ/ሪት ገነት በቀለ የጓሮ አትክልት በከፊል

በዚህም አሁን ላይ እያሳየች የምትገኘውን ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ መነቃቃትን መፍጠር በመቻልዋ በተሻለ ጥራትና ብዛት የጓሮ አትክልትን በማምረት ቤተሰቦቿ መመገብና የምግብ ዋስትናን በማስጠበቅ፣ እንዲሁም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በማስገኘት ምርቱን በተሻለ ብዛትና ጥራት ለማምረት ችላለች፡፡ ገነት ሁል ጊዜም የምትናገረው ይህ ፕሮጀክት ባይመጣና በይደግፋት ኖሮ የዚህን አይነት የአዕምሮም የተግባርም ለውጥ እንደማታመጣ ነው፡፡

<u>**ወ/ሮ ፎዚያ አደም**</u>፡-

ወ/ሮ ፎዚያ ወጣት፣ ባለትዳር፣ የቤት እመቤትና የሁለት ታዳጊ ልጆች እናት ስትሆን፤ ያለችበትን የወጣትነት ዕድሜና የወደፊት ህልም ልጆችዋን ለማሳደግና ቤተሰብዋን ለመንከባከብ ስትል መስዋትነት ከፍላ ሙሉ ጊዜዋን ሰጥታ በቤት ውስጥ የምታሳልፍ ሴት ናት፡፡ የተለያዩ ስራዎችን መስራት የምትችልበት ሰፊ ጊቢና አቅም ቢኖራትም የሚያበረታታትና የሚደግፋት አካል ስላልነበረ ለስራው ብዙ ትኩረት አትሰጠውም ነበር፡፡

በወቅቱ በነበረው የተጠቃሚ መረጣና የመጀመሪየው ስልጠና ላይ ተሳታፊ ባትሆንም ግን በጎረቤትዋ አማካኝነት የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ለመሆን ችላለች፡፡ ፕሮጀክቱን ዘግይታ ትቀላቀል እንጂ ባገኘችው ስልጠና፣ ልምድ ልውውጥ፣ የጎሮ አትክልት ዘርና የግብርና ቁሳቁስ ድጋፍ ቀድመው ከነበሩት ተጠቃሚዎች የተሻለ እንቅስቃሴና ውጤት አሳይታለች፡፡






ምስል 12፡ የወ/ሮ ፎዝያ አደም የጓሮ አትክልት በከፊል

የተደረገላት ድጋፍና ክትትል ከፍተኛ የስራ ሞራልና መነቃቃት የፈጠረላት ሲሆን ለቤተሰብና ለአካባቢው ህብረተሰብ እውቀትን ማጋራት፣ ከኬሚካል የፀዳ ተባይ መከላከያ (ፀረ-ተባይ)ና ቨርሚ ኮምፖስትን በመጠቀም በተሻለ ጥራት እና ብዛት የጓሮ አትክልትን ማምረት፣ ስራውን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግና፣ የቤተሰቡን የምግብ ዋስትና እጥረትን መከላከል ችላለች።

## 7.3. ቨርሚ-ኮምፖስት በከተማ ቆሻሻ ቅነሳ

ፔለም ኢትዮጵያ በምርጥ ተሞክሮ ማህበር አማካኝነት በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ላይ ከተገበራቸው ስነ-ምህዳርን የጠበቀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ አሰራሮች መካከል የቨርሚ-ኮምፖስት የማዳበሪያ አይነት ነው፡፡ ይህ የማዳበርያ አይነት የቨርሚ-ትሎችን በመጠቀም የሚዘጋጅ ሲሆን የአካባቢ ቆሻሻን በማስወገድ በኩልም ሆነ ተጨማሪም ጥቅሞችንም ይሰጣል፡፡ በወረዳው ይህ አዲስ አሰራር በመተግበር ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል አንዷ ወ/ሮ በለጡ ጣሰው ይባላሉ፡፡

ወ/ሮ በለጡ ጣሰው በግቢአቸው ውስጥ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች እና ፍርፍሬዎችን የተከሉ ሲሆን በየወቅቱ የተሻለ ምግብ እንዲያገኙና ጤናማ አትክልት ለማምረት እንዲችሉ በምርጥ ተሞክሮ አማካኝነት የወሰዱት ዘመናዊ የማዳበርያ አመራረትን በተመለከተ በተግባር የተደገፈ ስልጠናን ወደ ስራ በመቀየር ከሌሎች የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች በመቅደም በቤታቸው ውስጥ በሰለጠኑት መሰረት ተግብረውታል፡፡



ምስል13፡ የቨርሚ-ኮምፖስት ስራ

ወ/ሮ በለጡ ጣሰው እንደሚሉት ከሆነ ከዚህ በፊት የዚህ አይነት አሰራር ሰምተውም አይተውም አያውቁም፡፡ አሁን ግን በሰለጠኑት መሰረት የኮምፖስት ማዳበርያ ለማዘጋጀት አይቸገሩም፡፡ በግቢው ውስጥ

የሚጠራቀመው የቤት ጥራጊ፣ የፍራፍሬና አትክልት ልጣጭ፣ እንዲሁም በቤትና በአካባቢ የሚገኝ ማንኛውም የሚበሰብስ ነገር ለቨርሚ ኮምፖስት መስሪያነት ይጠቀማል፡፡ ሁኔታውንም ሲገልፁ እንዲህ ይላሉ "ቀደም ሲል ቆሻሻ የምንጥልበት ቦታ እንቸገር ነበር፤ ግቢው ይሸታል፣ ውሻና ድመት ይሰበሰቡበታል ምቹም አልነበረም፡፡

አሁን ግን እድሜ ለአዲሱ አሰራር ማዳበርያውን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገኝ ማንኛውንም በግቢያችን የሚበሰብስ ቆሻሻ በቀላሉ አይገኝም፡፡ ቆሻሻ እንደወርቅ ሆኗል ይላሉ" በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ማለት እንዲህ ነው፡፡

## 7.4. መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት

መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት ፔለም ኢትዮጵያ ካሉት አባል ድርጅቶች አንዱ ሲሆን ትኩረት አድርጎ የሚሰራውም በሴቶች ላይ ነው ማለትም መንገድ ላይ የወደቁ እንዲሁም ሰብሳቢ የሌላቸው ሴቶችን በመያዝና የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት እነሱን የማብቃት ስራ በመስራት ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ነው ተቀዳሚ አላማው፡፡ ይህንንም በማሳካት ዙሪያ ሁሉም ተጠቃሚዎች ሙሉ በሙሉ በድርጅቱ ውስጥ ታቅፈው ስለሚቆዩ ድርጅቱ ብዙ የተለያዩ ወጪዎች አሉበት፡፡ ከነዚህም አንዱ እለታዊ የምግብ ፍጆታ ሲሆን ይህም ካለው የኑሮ ውድነት አንፃር ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡




ምስል14፡ የመሰረት በጎ አድራጎት ድርጅት ሰራተኞች (ስልጠና (ሀ)፣ የመደብ ዝግጅት (ለ)፤ እና የጓሮ አትክልት ችግኝ ተከላ (ሐ))



ምስል15፡ የመሰረት በጎ አድራጎት ድርጅት የሰራው የጓሮ አትክልት ውጤት

ለዚህም አይነተኛ የሆነ መፍትሄ ለማግኘት በፔለም ኢትዮጵያ አጋዥነትና ደጋፊነት ስነ-ምህዳራዊ የጓሮ አትክልትን ለማምረት የሚያስችለውን የከተማ ግብርናን አተገባበር ዘዴ አስመልክቶ ተግባር ተኮር ስልጠና ለሚመለከታቸው የድርጅቱ ሰራተኞች ተሰጥቶ እንዲሁም አስፈላጊው የቁሳቁስ እና ሙያዊ ድጋፍ ተደርጎላቸው በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በየዕለት ምግባችን ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ የጓሮ አትክልቶችን በ2-3 ወር

ውስጥ ለማምረት እና ለመመገብ ችለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ጎመን፣ ጥቅል ጎመን፣ ቆስጣ እና ቀይስር ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሰፋ ያለ መሬት በመኖሩ በተወሰነ መልኩ ሰፋ አድርገው መስራት በመቻላቸው በሳምንት ለአትክልት መግዣ ይውል የነበረውን ወጪ ከመቀንስም አልፎ ንፁህና ጤናማ የሆኑ አትክልቶችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ አድርጓል ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ የአትክልት ተረፈ ምርቶችን በመጠቀም ማለትም እንደ ሽንኩርት፣ ድንች ልጣጭ የመሳሰሉትን በመጠቀም ቨርሚ ኮምፖስት ማምረት በመጀመራችው የአፈራቸውን ለምነት ጨምረው ምርትና ምርታማነታቸውን ከማስደጋቸውም ባሻገር አካባቢያቸውን ከብክለት ለመታደግ ችለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ድርጅቱን ለመጎብኘት የሚመጡ ብዙ ሰዎች በመኖራቸው የተሰራውን ስራ እንዲሁም የተገኘውን ውጤት ሲመለከቱ የስራ ተነሳሽነታችው እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ይህም ተግባር ድርጅቱን ከወጪ ከመታደጉም ባሻገር እንደ ሰርቶ ማሳያ መሆንም ችሏል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ያሉት ተጠቀሚዎች የከተማ ግብርና ስራ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው እነሱም በመሰልጠናቸው ከድርጅቱ በሚወጡበት ግዜም እንደ ስራ ፈጠራ ተጠቅመው እራሳቸው ኑሯቸውን ለማሻሻል እንዲችሉም አግዟቸዋል ብሎም በድርጅቱ ውስጥ ባሉበት ግዜ ትርፍ ግዜያቸውን አልባሌ ነገር ላይ ከሚያሳልፉ ይልቅ አስፈላጊውን እንክብካቤ ለአትክልቶቹ በማድረግ እንዲያሳለፉ መንገድ ከፍቶላቸዋል፡፡

## 7.5. ታዳጊ እና ወጣት ተማሪዎች

የ2012 እና 2013 ዓ.ም ለኢትዮጵያውን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ከባድ ዓመት ነበር፡፡ የችግሩ ድባብ እስካሁን ድረስ አለቀቀንም፡፡ በተለይ የወጣቶች ውሎ እና አዳር እቤት መሆኑ ከከባድነት አልፎ ጭንቀት ሆኖባቸው ነበር፡፡ በተወሰነ መልኩ አሁንም አለ፡፡ በተለይ የመጀመሪያው ወቅት ላይ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትን አስከትሎ በተፈጠረው የትምህርት ገበታ መቋረጥ የተፈጠረው ችግር ከባድ ነበር፡፡ ይህ ፕሮጀክት በዛን ወቅት ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ የራሱ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ የተፈጠረው ችግር ለሚከተሉት ሁለቱ አካላት በተለያዩ ምክንያቶች ልብ ሰብሯል፡፡ እነሱም፡-

### ለታዳጊ ህፃናት

እቤት አካባቢ ያሉ ህፃናት ከቤት ርቀው ለመሄድ እድሜያቸው ስለማይፈቅድ በማንኛውም ምክንያት ከግቢያቸው አይርቁም ነበር፡፡ ሆኖም ቤተሰብ ደግሞ ልጆቻቸው በግቢያቸው ያለውን የጓሮ አትክልት ሊያስነኩዋቸው አልፈቀዱም፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው ልጆቹ እንደ አጥፊ እንጂ የጓሮ አትክልት ጥቅም እና እንክብካቤ እውቀት ወይም ግንዛቤ እንዳላቸው ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡



ምስል 16፡ ህፃናት የተግባር ስልጠና ሲወስዱ



ምስል17፡ ህፃናት የልምድ ልውውጥ ላይ



ምስል18: ህፃናት የተግባር ሙከራ ሲያደርጉ

**ታዳጊ ወጣቶች**

በትምህርት መዘጋት ምክንያት እቤት አካባቢ መዋል የጀመሩ ታዳጊ ወጣቶች ቤት በመዋላቸው ከቤተሰብ ጋር መነታረክና በመጋጨት ነበር ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት።

ሆኖም ፕሮጀክቱ በሁለት ነገሮች በተሳካ ሁኔታ እነዚህ ታዳጊ ወጣቶችን ታድጓል። እነሱም፡-

- **አንደኛው፡-** የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወላጆች እና እድሜያቸው እስከ 12 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች የማነቃቂያ ልምድ ልውውጥ አብረው እንዲያደርጉ እና እንዲወያዩ ተደረገ። ልዩ ትኩረት የተሰጠው ታዳጊዎች ልምዳቸውን እና ትዝብታቸውን እንዲገልፁ ማድረግ ነበር። በዚህ ወቅት ህፃናቶቹ ሲናገሩ ቤተሰቦቻቸው እንደ አጥፊ እንጂ የጓሮ አትክልት ጥቅም እና እንክብካቤ ግንዛቤ እንዳላቸው ስለማይገነዘቡ የጓሮ አትክልት ቦታ ላይ እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም። በተቃራኒው ልጆቹ የጓሮ አትክልት ስራ እንደ ጊዜ ማሳለፊያ ይፈልጉታል።

ለዚህም ውጤት ማሳያ የሆነች ምሳሌ፡- ህፃን **ፍርዶስ** የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሆነችው የወ/ሮ ፎዚያ ልጅ ስትሆን የእናትዋን የአትክልት ስራና እንክብካቤ በማየት ወደ ስራው እየተሳበች የመጣችና የመስራት ፍላጎት ያደረባት ቢሆንም ታጠፋለች በሚል ፈፅሞ ወደ አካባቢው የሚያስደርሳት ሰው አልነበርም፡፡ የአብዛኛው የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወላጆች ችግር መሆኑን በመረዳት በተደረገው መሰረታዊ የጓሮ አትክልት ስልጠናና ትግበራ እንድትወስድ በማድረግ ዛሬ የራስዋን በማዳበሪያና በመሬት ላይ ውስን ቦታ በመያዝ ከወላጅ እናትዋ ጋራ በመሆን የራስዋን ጉልህ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ የምትገኝ ታዳጊ ነች፡፡

- **ሁለተኛው፡-** ወጣቶች እቤት መዋሉን እንደ መታሰር ስለሚያዩት ከቤት የሚወጡበት ምክንያት ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር ተሰባስበው የሚያወሩበት፣ የሚሰሩት ወይም ጊዜ የሚያሳልፉበት ወቅት/ሁኔታ ይፈልጉ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ምንም ነገር የላቸውም፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ፕሮጀክቱ የቤት ለቤት ዳሰሳ እና ቅስቀሳ ጀመረ፡፡

ለዚህም ውጤት ማሳያ የሚሆነ ምሳሌ፡- ታዳጊ በእምነት ሃይሉ በመጀመሪያ የከተማ ግብርና እውቀት እና ግንዛቤ አልነበረውም፡፡ ቢሆንም በኮረና ወረርሽኝ መጀመሪያ ወቅት ከአባቱ ጋር እቤት ይውሉ ነበር፡፡ በዚሁም አማካኝነት ውይይት በማድረግ የተወሰኑ ስራዎችን ወይም እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ወሰነ፡፡




ምስል19: በእምነት ቤተሰብ ግቢ ውስጥ (የፕሪም/ ሱስኒ ፍሬ (ሀ)፣ ግብርና ስራ ብቻ አይደለም መዝናኛም ነው (ለ)፣ ቆስጣ (ሐ))

መጀመሪያ በእምነት በቨርሚ ኮምፖስት ማዘጋጃ ሳጥን እንዴት እንደሚሰራ በተማረው መሰረት ከስራ በኋላ አባቱ ደግሞ የቨርሚ ትል አመጣለት፡፡ አሰራሩንም ካሳየው በኋላ ቨርሚ ኮምፖስት ከመስራት አልፎ የቨርሚ ትል መሸጥ ጀመረ፡፡ ሁለተኛ አትክልቶች (እንደ ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ቲማቲም፣ ቃርያና የመሳሰሉትን) የቨርሚ-ማዳበሪያን በመጠቀም ማምረት ችሏል፡፡ ሶስተኛ እራሱ የዶሮ ቤት በመስራት ከ12 ዶሮዎች በየቀኑ 8-10 እንቁላል ያገኛል፡፡ የበእምነት ወላጆች ሲናገሩ ከዚህ በኋላ አያቆምም ልምዱም ለኋላ ህይወቱ ይጠቅመዋል ይላሉ፡፡

- ስለሆነም የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ እምነት በማሳደር ልጆች አላስፈላጊ ቦታ ከመዋልና አላስፈላጊ ስራ ከመስራት እንዲቆጠቡ እና ከዚህ በተቃራኒ እራሳቸውን በስራ በመጥመድ ብርቱ ስራ ወዳድ ዜጋ በመሆን ቤተሰባቸውንና አካባቢያቸውን እንዲደግፉና እንዲያግዙ ማድረግ ተችሏል፡፡

- ልጆች ስልጠና እንዲወስዱ ከማድረግ ባሻገር እርስ በርሳቸው በከተማ ግብርና ላይ የእርሰ በርስ ልምድ ልውውጥ፣ የኤክስቴንሽን ስራ በመስራት ለራሳቸው እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ልዩ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡
- የአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም የከተማ ፅዳትና ውበትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለውን ቨርሚ ኮምፖስት በመጠቀም የአትክልት ማዳበሪያን በማምረት ለራስ የመጠቀምና ለሌሎች እውቀትን በማስተላለፍ የምርቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማስቻል ተችሏል፡፡
- እንዲሁም ትክክለኛ፣ ውጤታማና አኩሪ የሆነ የቨርሚ ኮምፖስት ምርትን በማምረትና ለህብረተሰብ በማከፋፈል የገቢ ምንጭ የማግኘት አቅምን ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ህፃናት እና ወጣቶች በመሰረታዊ የጓሮ አትክልት እውቀት፣ አሰራርና አተገባበር ማወቅ መቻል፣ የራስ እውቀትንና ፈጠራን በተለያየ መንገድ ማሳደግና ማጎልበት መቻል፣ በከፍተኛ ደረጃ የአዕምሮ መነቃቃትን መፍጠር መቻልን አሳይቷል፡፡

# 8. ከፕሮጀክቱ ምን ተማርን

የከተማ ግብርናን በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በወረዳ እንዲሁም በዓለም ደረጃ መተግበር በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ በየካ ክፍለ ከተማ ላይ ከተተገበረው የከተማ ግብርናም የሚከተሉትን ነጥቦች መማርና መገንዘብ ችለናል፡፡

- የከተማ ግብርናን መተግበር በሁሉም የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የምግብ ዋስትናን አስመልክቶ ላለባቸው ችግሮች አፋጣኝ የሆነ መፍትሄ መስጠት ይችላል፡፡ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ስንል ወጣት፣ አዛውንት፣ ሴቶች፣ የኑሮ ደረጃ፣ የመሬት ይዞታን ስራ አጥነትን በምንም ሁኔታ ሳይለይ ለሁሉም እኩል የምግብ ዋስትናን አስጠብቆ የኑሮ ውድነትን፣ ድህነትን በተወሰነ መልኩ ለማሻሻል ጉልህ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡
- የከተማ ግብርናን መተግበር የሚሰጠው ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም ለረጅም ግዜ በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረው ግንዛቤ ግን ዝቅተኛ የነበረ መሆኑንም ተረድተናል፡፡
- ከፕሮጀክቱ የተማርነው ነገር ቢኖር የመሬት እጥረት፣ እና የሚታየው የውሃ እጥረት እንደ ትልቅ ችግር እንደማይቆጠር ነው ምክንያቱም አነስተኛ የመሬት ይዞታን እንዴት መጠቀም እንደምንችል የሚያመለክቱና የሚያስተዋውቁ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች እየመጡ ስለሆነ እንዲሁም የውሃ እጥረትን አስመልክቶ ቤት ውስጥ ቆሻሻ ነው ብለን የምናስበውን ውሃ መልሶ መጠቀም የሚያስችሉ ዘዴዎችም ተገንዝበናል፡፡
- ሌብነት የከተማ ግብርናን በመተግበር ውስጥ ከሚያጋጥሙ ችግሮች አንዱ ቢሆንም እንዳንድ ጠንካራ ሰዎች በስርቆት የተሰማሩ ሰዎችን በማስተማርና በማሰልጠን ወደ ትግበራ እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሚቻል ተምረንበታል፡፡
- በአብዛኛው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች በተለይም ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ለመዝናኛ የሚሆኑ ቦታዎችን ማግኘት በጣም ከባድ ነው፤ ነገር ግን ኑሯቸውን አዲሰ አባባ ውስጥ ያደርጉ የተለያዩ ነዋሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት በአካባቢያቸው አነስተኛ የሆኑ

ለመዝናኛነት መሆን የሚችሉ እንዲሁም በተዘዋዋሪ የብዝሃ ህይወትን ማስጠበቅ የሚችሉ ቦታዎችን መፍጠር እንደሚችሉ ተገንዝበናል፡፡

# 9. ማጠቃለያ እና ምክረ-ሃሳብ

## 9.1. ማጠቃለያ

በዘላቂነት የከተማ ግብርና አተገባበርን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው የመንግስት ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች፣ አምራች ገበሬዎች እንዲሁም ወጣቶች ጋር ጥሩ ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ህብረተሰቡ በሚያመቸው መልኩ ሁሌም በግቢው ውስጥ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን እንዲያመርት ማድርግ በአትክልት አቅርቦት ላይ ሊኖር የሚችለውን ችግሮች በእጅጉ መቀነስ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የከተማ ግብርናን በማዘመን መተግበር ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብሎም አካባቢያዊ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ትኩረት ሰጥቶ ሊተገብረው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ለተግባራዊነቱም በጋራ መቆም ይገባል፡፡

## 9.2. ምክረ ሃሳብ

- የከተማ ግብርና ፅንሰ ሃሳብን እንደ አንድ የከተማ ልማት ፕሮግራም በመቀበል የከተማ ልማት እቅድና መመሪያ ውስጥ ማካተት ዘርፉ በተሻለ ሁኔታ እንዲተገበርና የከተማ ልማት ስራዎችንም ለማፋጠን ይረዳል፡፡
- የተለያዩ አዳዲስ የምርምር ዉጤቶች፣ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ አጋዥ የሆኑ ስልጠናዎችን መስጠት የከተማ ግብርናን ለማስተዋወቅና በስፋት ለመተግበር አይነተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡
- የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መተግበር የተሻለ ውጤት ለማስገኘት ያግዛል፡፡
- የከተማ ግብርናን ከገበያ ጋር እንዲሁም አነስተኛ ከሆኑ የግብርና ማቀነባበሪያ ጋር ማስተሳሰር የምርት እሴቱን ከመጨመር አንፃር ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው፡፡

- የከተማ ግብርና አተገባበር መመሪያዎችን በትክክል ከተገበርን በአካባቢ ብሎም በሰው ልጆች ጤና ላይ ሊመጣ የሚችለውን የጎንዮሽ ጉዳት በእጅጉ መቀነስ እንችላለን ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የከተማ ግብርና ስራዎች የአካባቢ ብክለትን በመቀነስ ጤናማ እና ንፁህ አትክልቶች ማቅረብ ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

## 10. ማጣቀሻ


- BPA, 2020: Annual Report of 2020, Best Practice Association
- Jenifer Cockrall King, 2012: Food and the City: Urban Agriculture and New Food Revolution
- Mhiteme Feleke Debela and Akalewold Fedilu Mohammod, 2020: The Role of Urban Agriculture in Improving the Livelihood of the Urban Poor and Challenges: The case of Hawassa City Administration, SNNPRS Ethiopia.

## ፔለም ኢትዮጵያ

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሚያዚያ 27 2016 በአባል ድርጅቶቹ አማካኝነት የተመሰረተ ሃገር በቀል ድርጅት ነው፡፡ ፔለም (PELUM) የሚልው ቃል የእንግሊዘኛ ምህፃረ-ቃል ሲሆን ትርጓሜውም አሳታፊ ስነ-ምህዳራዊ የመሬት አጠቃቀም አያያዝ ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ፔለም ኢትዮጵያ 13 አባል ድርጅቶች አሉት፡፡ ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም የፔለም አፍሪካ አሶሴሽን አባል ነው፡፡

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም ዓላማ ስነምህዳርን እና ብዝሀ-ሕይወትን በመንከባከብ ምግብ ዋስትናው በዘላቂነት የተረጋገጠለት ማህበረሰብ እንዲኖር አባላት እንዲያውቁ እና እንዲተገብሩ ማገዝ እና ዓቅም መገንባት ነው፡፡ እንዲሁም የአካባቢ እና የህብረተሰብ ጤናዎች እና ስራዎች የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ስራቸው የተሳካ እንዲሆን እና መብታቸውን እንዲያውቁ እና እንዲከራከሩ ማገዝ ነው፡፡

ፔለም ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ከብሬድ ፎር-ዘ ዎርልድ (ምግብ ለዓለም) በተገኘ ድጋፍ አማካይነት በሀገሪቷ በሚገኙ ስድስት ክልሎች (አፋር፣ ቤኒሻንጉል፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ እና አማራ) እና አንድ የከተማ አስተዳደር (አዲስ አበባ) ላይ በአባል ድርጅቶቹ አማካኝነት የተሳካ እና አብነት የሚሆን የስነ-ምህዳራዊ ግብርና ስራ እንዲኖር እየሰራ ይገኛል፡፡ ስነ-ምህዳራዊ ትግበራ ማለት ከግብርና ስራዎች ጋር በተያያዘ በሰዎችና በአካባቢያቸው ሊደርስ የሚችለውን የጎንዮሽ ጉዳት ለመቀነስ ግብርናውን ከስነ-ምህዳራዊ መርሆችን ጋር በማዋሀድ እንዲተገበር የሚያግዝ ትግበራ ነው፡፡ ዋና አላማውም ብዝሐ ሕይወትን፣ አካባቢንና የተፈጥሮ ሃብትን ለዘላቂ ልማት ለማስጠበቅ፤ ሰው ሰራሽ ግብአቶችን በመጠቀም ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችሉ አደጋዎች መጠበቅ ነው፡፡

## በፔለም ኢትዮጵያ ትብብር የታተሙ ፅሁፎች

1. Some examples of best practices by smallholder farmers in Ethiopia ( 3 with Best Practices Association and Prolinova))
2. Trench gardening for vegetable Production in arid and Semi-arid aseas (2019)
3. የዝናብ አጠር ስነ-ምህዳራዊ ግብርና ተሞክሮ በኮነባ ወረዳ (አፋር) (2013 ዓ.ም.)

## የአሁኑ እትም

1. ስነ-ምህዳራዊ የከተማ ግብርና መልካም ተሞክሮ በአዲስ አበባ

## ቀጣይ እትም

1. ልውጥ ህያዋን (GMO) በተመለከተ …
2. Challenges and opportunities of agro-ecological practices in the Horn of Africa

## ለበለጠ መረጃ ድረ-ገፃችንን ይጎብኙ

https://www.pelumethiopia.org.et

# ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም

ፔለም ኢትዮጵያ የአባል ድርጅቶቹን አቅም በማሳደግ እርስበርሳቸው እንዲተሳሰሩና እንዲገናኙ በማድረግ በዘላቂ የገጠርና የከተማ ግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ ፔለም ኢትዮጵያ በሀገራችን ውስጥ የነዋሪውን ህዝብ የመመገብ ሸክም እና ሀላፊነት በአርሶ እና አርብቶአደሮች ትከሻ ላይ ነው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ አርሶ እና አርብቶ አደሮቻችን ምርታማነትና ውጤታማነት ካላሻሻልን የሀገሪቱን ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ስለዚህ በከተማ ላይ ያለውን የከተማ ህብረተሰብ የምግብ አቅርቦት እና ጤናማነት ትኩረት እንደሚያስፈልገው በማመን በፕሮጀክት መልክ ለውጤታማነቱ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ስለዚህ ፔለም ኢትዮጵያ የጋራ ጥረቶቻችንን በማስተባበር፣ የተለያዩ ዘዴዎችንና ልምዶችን በመጠቀም አባል ድርጅቶቻችን በሀገሪቱ የልማት ስራዎች እንዴት መከወን እንዳለባቸው ተፅእኖ ለመፍጠር የሚያስችለው የተቀናጀ አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት አንዱ ነው፡፡ ለዚህም ነው ይህ መፅሃፍ የያዘው መልካም ተሞክሮ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ላይ እና በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ በመሰረት በጎ አድራጎት ድርጅት ውጤታማ በሆነ ፕሮጀክት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ብሬድ ፎር ዘ ወርልድ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በዚሁ ፕሮጀክት ላይ የተጠቃሚዎችን ኑሮ በማሻሻል በኩል እንዲሁም ይህ ስራ በስኬት እንዲጠናቀቅ ለማስቻል ላበረከተው የገንዘብ ድጋፍ ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም ታላቅ ምስጋና ያቀርባል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን